# ኤርምያስ ለገሰ ሰመረ አለሙ

ኤርምያስ ለገሰ ቀደም ባለዉ ጊዜ ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ለህወአት መንግስት ተቀጥሮ ሲሰራ ከቆየ በሁዋላ መዉጫዉን እንዳገኘ ከሞቀዉ ወምበሩና ከደመቀ ክብሩ ተነስቶ ወደ ሀገረ አሜሪካ ኮብልሎ መጠለያ ሲፈልግ እዉር ድምብሩ የጠፋባቸዉንና ታዋቂ ኢትዮጵያንን አነፍንፎ በመጥለፍ የተካነዉ የግምቦት 7 ሀይል ላይ ወደቀ። እንግዲህ ልብ በሉ ለሀገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ የሆነ ሰዉ ግምቦት 7 ያቀረበለትን ፍቃድ አሰጥሀለሁ የሚለዉን አማራጭ የሌለዉን ምርጫ ተቀብሎ በግምቦት 7 ቅኝት ኢሳት በሚባለዉ የዜና ተቋም ገብቶ ኢሳትን ነብስ ዘራበት በምሁራዊ አስተያየቱና ትንታኔዉም የዜና ተቋም መልክ አስያዘዉ።

ታዲያ ጊዜያቶች እያለፉ ሲሄዱ ኤርምያስ ለገሰና መሰሎቹ ኢሳት ዉስጥ ያለዉ ነገር ስላልጣማቸዉ ኢሳትን ጥለዉ ኢትዮ 360 የተባለ የሚዲያ ተቋም ከፈቱ። ኢትዮ 360ም በኤርምያስና በባልደረቦቹ የፖለቲካ ትንታኔ የወያኔን አካሄድ ዱካ ዱካዉን እየተከታተሉ በማጋለጥ፤ ኤርምያስም የአይን እማኝነቱንና ዉስጥ አዋቂነቱን በመጠቀም የሰጠዉ ምስክርነትና ትንተና የተመልካችና የአድማጭን ቀልብ በመሳቡ የሚዲያዉ ተከታታዮች ከእለት ወደ እለት እያሻቀበ ሄደ። ይህም አካሄድ ኢሳትና ግምቦት 7 አካባቢክፉኛ መደናገጥን ፈጠረ። ኢትዮ 360 የሀገራችንን ፖለቲካ በመግራት፤ የህወአትን አሰራር በማጋለጥ፤ ህወአት ሊያደርግ ያቀደዉን ቀድሞ በምሁራዊና በፖለቲካዊ እይታ ለህዝብ በማሳጣት፤ እዉቅ ምሁራንና ሀገር ወዳድ የአንድነት ሀይሎችን በመጋበዝ፤ እይታቸዉን ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያጋሩ በማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ አደረገ። እንደሚባለዉ የኢትዮጵያ ሚኒስተሮችም ከተራዉ ህዝብ ባላነሰ ማስታወሻ እየያዙ እንደሚከታተሉ ከሀገር ቤት የሚደርሱ መረጃዎችም ይጠቁማሉ ያለባቸዉን የእዉቀት ክፍተት ለመድፈንም ኢትዮ 360ን በቋሚነት ይታደማሉ። በቅርቡ እንኳን የአባይ ድርድር ከአሜሪካኖች እጅ ወጥቶ ኢትዮጵያ ሚዛን ያላት ተደራዳሪ የሆነችበት (game changer) በኢትዮ 360 ባላሰለሰ ጥረት እንደ ነበር አንባቢ ወደ ኋላ ተጉዞ ስለ አባይ የተደረጉትን ዉይይቶች ከድረ ገጹ መመልከት ይቻላል።

እንግዲህ ኤርምያስ ለገሰ የኢትዮ 360 የስበት ማእከል ተደርጎ ከተወሰደ በኋላ ወደ ኤርምያስ ለገሰ **የሚወረወረዉ ድንጋይ እየበረታ መጥቷል** ይህም ባመዛኙ ከግምቦት 7 ደጋፊዎች፤ከወያኔዎች ፤ አክራሪ ኦሮሞዎች አልፎ አልፎም ከሻቢያም አካባቢ አንዱ ሲያርፍ ሌላዉ እየተቀበለ የእሩምታ ተኩስ በኤርምያስ ማዘነብን ቀጥለዋል። ኤርምያስ ላይ እንዲህ ጥቃቱ መበርታቱ አድራጊዎቹ የራሳቸዉ ምክንያት ቢኖራቸዉም ዋናዉ ግን ኤርምያስ እግባቸዉ እንዳይደርሱ ደንቃራ በመሆኑና የአንድነት ሐይሉም ኤርምያስን በብቃት መከላለከል ባለመቻሉ ነበር። ይህ አሰራር ቀደም ሲል በፕሮፌሰር ሐይሌ ላሬቦ ላይ በተከታታይ ታይቷል። ቆንጨራ መፍትሄ ባልሆነበት አለም እዉቀትና ኢንፎርሜሺን ከምንም በላይ ዋጋ ያለዉ በመሆኑ ኤርምያስም በዚህ የታጠቀ በመሆኑና ያለበት አገርም ሰዉ ባስተሳሰቡና ባመለካከቱ የማይገደልበት ከመሆኑም ባሻገር ህገ መንግስቱም ሆነ የህግ ተቋሙ ለኤርምያስ ጥበቃ ስለሚያደርጉለት ኤርምያስ በባላንጣዎቹ ሰይፍ ሊወድቅ አልቻለም ይልቁንም ህገ መንግስቱ ያሻዉን እንዲናገር አመቻቸለት።

ኤርምያስ ለገሰ ከትግሬ ፋሺስቶች ጋር አብሮ ሰርቷል እሱም ይህንን አልካደም ይህም የሚደበቅ አይደለም። ትምህርት በጨረሱ ማግስት ስራ በዘር መስፈርት ብቻ በሚቸርበት አገር እንዲህ ያለን ግብዣ ላለመቀበል የሚያንገራግሩ ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ እነሱም የራሳቸዉ ምክንያት ሊኖራቸዉ ይችላል። የኤርምያስ ከህወአት ጋር አብሮ መስራቱ ዛሬ ላይ ምን ያህል እንደጠቀመን ማስተዋል የተቸረዉ ዜጋ ሊያገናዝብ ይገባል።ኤርምያስ በህወአት ቤት የተሰራዉን ግፍ ሳያነሳ ያለፈበት አንድም ጊዜ የለም ይህንንም በጽሁፍ፤ በመጽሀፍ፤በዉይይት ቀርቦ ተመልክተናል የወያኔን ቤትም እርቃኑን ካስቀሩት እዉቅ ዜኖች መሀል ኤርምያስ ለገሰ ዋናዉ ነዉ። ኤርምያስ በኢሃደግ ቤት ኑሮ ቢደላዉም አጋጣሚዉን ሲያገኝ ስርአቱን ከድቶ በስደት መኖርን መምረጡ ነዉ። በሱ ደረጃ ያንን ክብርና ጥቅሙን ትቶ የከዳ ሚኒስተር አልተመለከትንም። ብዙዎቹ እንደ ኤርምያስ ወደ ባህር ማዶ ወጥተዉ ነበር ነገር ግን በሀገር ቤት የሚያገኙት ጥቅም በልጦባቸዉ እየተግተለተሉ ተመልሰዋል። የህወአትን ስርአት በመነቅነቅ ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦ ካደረጉት ዜኖች መሀል ኤርምያስ ለገሰ አንዱ ነዉ በእርግጥ ፕሮፌሰር ጌታቸዉ ሐይሌ፤ አቻምየለህ ታምሩ፤አቶ ጌታቸዉ ረዳ(ኢትዮ ሰማይ) ፕሮፌሰር ሐይሌ ላሬቦ፤ሻለቃ ዳዊትን የመሳሰሉ ታላላቅ ዜኖችን ሳንረሳ ማለት ነዉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ታምራት ላይኔ፤አረጋዊ በርሄ፤ አንዳርጋቸዉ ጽጌ የመሳሰሉት ከሱ በተሻለ ሁኔታ ስርአቱን በመቅረጽ የተሳተፉና ለአመራሩ ቅርበት የነበራቸዉ ያለመታደል ሁኖ ካወቁት በጥቂቱ ከመንገራቸዉም ባሻገር አቀራረባቸዉም ተቃርኖ የተሞላበትና የፖለቲካ ትርፍ ማግኛ ብቻ ነበር ።

አንድ ህዝብ በኢንፎርሜሺንና በእዉቀት ካልታጠቀ የጋራ የሆነ ግንዛቤ አግኝቶ ለጋራ አላማ ሊሰለፍ አይችልም ያንን ክፍተት ኤርምያስ በመጽሀፉና ከኢትዮ 360 ጓዶቹ ጋር በመሆን የአንድነት ሀይሎችን በማጋበዝ ህዝባችንን ግንዛቤ አስጨብጧል በዚህም አስተዋጽኦዉ እዉቅና ሊሰጠዉ ይገባል ።

አንዳርጋቸዉ ጽጌ በህወአት ተገፍትሮ እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ ህወአት ሲደናበር በአዲስ አበባ ልጅነቱ ወያኔን ጣቱን ይዞ መስመር አስይዞ፤ ከህዝብ አስተዋዉቆ የወጣ የግምቦት 7 መሪና የኢዜማ የመጋረጃ ጀርባ ሰዉ ከመሆኑም ባሻገር ህወአት ወደ አገር ቤት ከመግባቱ በፊት በሎንዶን መንገዱን ሲያጸዳለት፤ ስብሰባ ጠርቶ ለህወአት በጎ በጎዉን በማስታወቅ የማይረሳ የህወአት ባለዉለተኛ መሆኑን ዛሬ ላይ ለረሱት ማስታወሱ ግድ ይላል። በአንድ መጽሄት ቃለ ምልልሱ ብዙ መጽሀፍ ከማንበብ አቶ መለስ አጠገብ መቀመጥ ብዙ እዉቀት ይሰጣል ከማለቱም ባሻገር ከሙቶ አለቃ አያልሰዉ ደሴ ጋር ባደረገዉ ቃለ ምልልስ የሙቶ አለቃ አያልሰዉ ደሴ በኢትዮጵያ አንድነት ከማያምን ድርጅት ጋር አንድነት የለኝም አብሬዉ አልሰራም ብለዉ ፈርጥመዉ ሲመልሱ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ግን ግዛዉ ከሚባል የኢሳት ምንደኛ ጋር የሙቶ አለቃ አያልሰዉ ደሴን በክንድ ጠምዝዞ ዉይይት ምን ያህል እንደ ተጫናቸዉ አንባቢ ይህንን ከሊፐ ጎግሎ መመልከት ይችላል https://www.youtube.com/watch?v=nkSwl_eexCk ይህ ከሊፐ ከሰባቱ ክፍል ሶስተኛዉ ነዉ። ግዛዉ አንዳርጋቸዉን ለማስደሰት ድርጅቱ ያሰበዉንም አላማ ለማሳካት ምን ያህል ከመስመሩ ወጥቶ እራሱን ሲያሳጣና ከጋዜጠኛ ስነ ምግባር በማፈንገጥ ዋና ተከራካሪ በመሆን፤ በመሪ ጥያቄ(leading question) አቅጣጫን በማሳት፤ መልስን በማቋረጥ፤ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆን ለሙያዉ ሳይሆን ለግምቦት7 ግልጋሎት እንደዋለ ማስታወስ እንወዳለን። አሱም ለመማር ዝግጁ ከሆነ ዳግም ያንን ከሊፐ እንዲመለከተዉ እንመክራለን። ለወደፊትም እራሱን ችሎ እንዲቆም እናሳስባለን ሙያዉ ጋዜጠኝነት እንጅ ካድሬነት ካልሆነ።

**ክብር ለሙቶ አለቃ አያልሰዉ ደሴ ኢትዮጵያ በጨለመባት ጊዜ የአንድነት ሐይሉን በመወከል የመልካም ዜጋ አርአያ ሁነዋል የዜግነት ግዴታዎንም ተወጥተዋል እንደ እርሶ አይነት ዜጋ ያብዛልን።**

ፖለቲካችን በሆያ ሆዬ ላይ ብቻ የተመሰረተ ካልሆነ በስተቀር አይነኬዎችን እየተዉ ተጋላጭ የሆኑ ወገኖች ላይ ፍላጻ ማንሳት አግባብ አይሆንም። እነ ስዩም ተሾመ ፍርድ ቤትም በአነቃቂ ነገሮች ሞቅታ የሚብጠለጠሉ የሀገር አሳቢ ዜጎችንም እረፍት ስጡልን የሚል ወገን ያስፈልጋል። እነሱ ድርጅታችን ተነካ መሪያችን ተነካ ብለዉ መድረኩ ላይ ሲጋልቡ ልጓም ካልተበጀላቸዉ እራሳቸዉንም አሳስተዉ ሌላዉንም ያሳስታሉ ሀገርም ይዋከባል። በዚህ አይነት የስብጥር ተኩስ በአላዋቂዎች ግልቢያና ዘለፋ ለአለም የሚበቁ ምሁራንና ልምድ ያላቸዉ ኤክስፐርቶች ከባለጌዎች ጋር ሜዳ ላለመዉረድ እዉቀትና ልምዳቸዉን ይዘዉ ከወገን ተራርቀዋል እነሱ በመራቃቸዉ ሜዳዉ ላይ አላዋቂዎች ይፈነጩበት ይዘዋል። በዚህ በተቀነባበረ ጥቃት ሰለባ ከሆኑት መተኪያ ከሌላቸዉ ወገኖች መሀል **ዶ/ር ታየ ወልደ ሰማያት ይገኙበታል።** በእርግጥ በፕሮፌሰር ሐይሌ ላሪቦ ላይ ተከፍቶ የነበረዉ ጦርነት በወገን እርዳታ ወደ ቦታዉ እንዲመለስ ተደርጓል የአንድነት ሐይሉ ሲነካ ወገን ባለ በሌለ ሀይሉ ተሰልፎ መመከቱ ብዙ ጀግኖችን እንድናፈራ ያደርገናል።

በአጠቃላይ በኤርምያስ ላይ የተነጣጠረዉ መዳረሻ ግቡ ኤርምያስ በተናጥል ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ላይ ነዉ። **ኤርምያስ ለገሰ ምሁር ጋዜጠኛና ደራሲ ነዉ።** ኤርምያስ ዛሬ አለም እጁን ዘርግታ ልትቀበለዉ የምትችል ዜጋ ነዉ ቢያንስ ቢያንስ እነ ሰየ አብረሀን፤ ቴድሮስ አድሀኖምን የተቀበለ አለም አቀፉ ድርጅት ኤርምያስ ባለዉ ልምድና እዉቀት እጁን ስሞ ሊቀበለዉ እንደሚችል መገመት አይከብድም። ኤርምያስ 24/7 ቤተ ሰቡን ኑሮዉን ትቶ ኢትዮጵያን ማገልገሉ ምክንያት እየተፈለገ የሚጠለጠልበት ምክንያት ስለማይኖር የአንድነት ሀይሉም ለሀገሩ የሰጠዉንና ወደፊት የሚሰጠዉን አገልግሎት በማመዛዘን ጠንካራ ድጋፉን ሊሰጠዉ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን እንደ ኤርምያስ ለአንድነት የቆሙ ወገኖች ከጠላት በሚተኮስባቸዉ ሚሳይል መድረኩን እየለቀቁ ተንታኞቻችን እነ ስም አይጠሬዎች ፖለቲካዉን ከማቆሸሺ አልፈዉ የሌሎችን አስተሳሰብ ስለሚመረዙ ወጣቱ ያለ መሪ ይቀራል የሚል ስጋት ይኖራል። ዛሬ **ኤርምያስ ላይ የተነጣጠረዉ ነገ ኢትዮ 360፤ አቻምየለህ ታምሩ፤ መስከረም አበራ፤ተመስገን ደሳለኝ፤ አቶ ጌታቸዉ ረዳ(ኢትዮ ሰማይ)፤ ጋዜጠኛ ታምራት ነገራ፤እስክንድር ነጋ** ላይ ይሆንና ኅመን በጤና የሚለዉ ወገን ይበዛል።

*ባጠቃላይ የጽሁፉ አላማ ኢትዮጵያን ብለዉ የተነሱ ወገኖች በቀጥታና በተዘዋዋሪ የስነ ልቦና ጥቃት በረቀቀ መንገድ በጸረ ኢትዮጵያ ሐይሎችና ማናዣብ በከበዳቸዉ ወገኖች ሲደርስባቸዉ ሀገር ወዳዱና የአንድነት ሀይሉ ዝም ብሎ ከመመልከት ይልቅ በተቻለዉ ሁሉ አጋርነቱን ቢያሳይ ኢትዮጵያዊነት ተከብሮ አብቦ ይቆያል ከሚል ግንዛቤ ነዉ። ይህ ካልሆነ ግን መምህር፤ መሪና፤ ግምባር የሚሰጥ ጀግና እያጣን ዘወትር ተዋራጂ መሆናችን አይቀሬ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንድ አስተዋጽኦቸዉ የጎላ ዜጎች በአንድ ወቅት ከምናዉቃቸዉ መስመር ወጡ በሚል እሳቤ ባልተመጣጠነ ትችት ሰብአዊ ክብራቸዉ እንዳይወርድ ጥንቃቄ*

*ማድረግ ያስፈልጋል። ተቃርኖም ካለ በዉስጥ መስመር ግንኙነት ቢደረገ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ከመሆኑም ባሻገር ለኢትዮጵያ ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል ብለን እንገምታለን ከነዚህ የሀሳብ ባህሮች መሀል ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤ ዶር ዳኛቸዉ አሰፋ፤መምህር ታየ ቦጋለ ይገኙበታል። በነገራችን ላይ የዚህ ጽሁፍ ጸሃፊ ከዚህ በፊት ኤርምያስ ለገሰ ኢሳት ቤት በነበረበት ጊዜ ካልተመቹት መሀል አንዱ ቢሆንም ዛሬ ላይ ለሀገሩ የሰጠዉን ጥቅም በማገናዘብና ከግምት በማስገባት እይታዉን መለወጡን ይገልጻል።*

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር **semere.alemu@yahoo.com**